የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን
Ethiopian Capital Market Authority

# የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን የክፍያ መመሪያ ቁጥር 996/2016

ፀየኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን

መጋቢት/2016 ዓ.ም

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች እና የሥራ ወጪውን ለመሸፈን ተመጣጣኝ የአገልግሎት ክፍያ እንዲወስንና ከካፒታል ገበያ ተሳታፊዎች እንዲሰበስብ በካፒታል ገበያ አዋጅ ስልጣን የተሰጠው በመሆኑ፣

በባለሥልጣኑ የሚሰበሰበው ክፍያ ግልጽና ለህዝብ ተደራሽ መሆን አስፈላጊ በመሆኑ፣

ባለሥልጣኑ በካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 አንቀጽ 108 (2) መሠረት ይህንን መመሪያ አውጥቷል።

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "የካፒታል ገበያ ባለስልጣን የክፍያ መመሪያ ቁጥር 996/2016" ተብሎ ሊጠራ ይችላል።

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር፡-

1. **"የማመልከቻ ክፍያ"** ማለት ለሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ ወይም ለፈቃድ ማመልከቻ በአመልካች ለአንድ ጊዜ የሚከፈልና የማይመለስ ክፍያ ነው።

2. **"ባለሥልጣን"** ማለት በካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 የተቋቋመው የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለሥልጣን ነው።

3. **"የካፒታል ገበያ ግብይት"** ማለት በሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ፣ ባልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ወይም በሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያዎች የሚደረግ ማንኛውም ግብይት ነው።

4. **"የኩባንያ ቦንድ"** ማለት የሱኩክ ቦንድን ጨምሮ በአክሲዮን ኩባንያዎች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በአለማቀፍ ተቋማት ለሽያጭ የሚወጣ ቦንድ ነው።

5. **"የቋሚ ገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ"** ማለት የኩባንያ ቦንዶችን እና የአካባቢ አስተዳደር ቦንዶችን ጨምሮ ለሽያጭ የሚወጣ የብድር ሰነደ ሙዓለ ንዋይ ነው።

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን

6. **"የፈቃድ ክፍያ"** ማለት የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ፣ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ የፈቃድ ማመልከቻ ሲፀድቅ ለባለሥልጣኑ የሚከፈል የአንድ ጊዜ ክፍያ ነው።

7. **"የፈቃድ እድሳት ክፍያ"** ማለት የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ፣ የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ፣ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ፈቃድ ሲታደስ ለባለስልጣኑ የሚከፈል ዓመታዊ ክፍያ ነው።

8. **"የገበያ መሰረተ ልማት አገልግሎት ሰጪ"** ማለት ፍቃድ የተሰጠው የሰነደ ሙዓለንዋይ ገበያ፣ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ እና የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ነው።

9. **"የአካባቢ አስተዳደር ቦንድ"** ማለት አግባብነት ባለው ህግ የብድር ሰነደ ሙዓለንዋይ እንዲያወጣ እና ለህዝብ ሽያጭ እንዲያቀርብ ስልጣን በተሰጠው የክልላዊ መንግስት፣ የከተማ አስተዳደር ወይም ሌላ የመስተዳደር አካል የሚወጣ ቦንድ ማለት ነው።

10. **"አዋጅ"** ማለት የካፒታል ገበያ አዋጅ ቁጥር 1248/2013 ነው።

11. **"የምዝገባ ክፍያ"** ማለት በአዋጁ አንቀጽ 75 መሠረት ሰነደ ሙዓለ ንዋዮች በባለስልጣኑ ሲመዘገቡ የሚከፈል ክፍያ ነው።

12. **"የግብይት ክፍያ"** ማለት ፈቃድ ባለው የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ፣ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ ወይም የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ ላይ በሚደረጉ በእያንዳንዱ ግብይቶች ላይ የሚተገበር ባለሥልጣኑ የሚያስከፍለው ክፍያ ነው።

13. "ሱኩክ ቦንድ" ማለት የሼሪአ መርሆዎችን እና የእስልምና ህጎችን የተከተለ የብድር ሰነደ ሙዓለንዋይ ነው።

14. በዚህ መመሪያ የተገለጸ ማንኛውም ቃል ወይም ሐረግ በአዋጁ የተሰጠው ትርጉም ይኖረዋል፡፡

**3. የተፈጻሚነት ወሰን**

ይህ መመሪያ ማናቸውም የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ምዝገባዎች፣ የፈቃድ ማመልከቻዎች እና የካፒታል ገበያ ግብይቶች ላይ ተፈጻሚ ይሆናል።

**4. መረጃ መሰብሰብ እና ሪፖርት ማድረግ**

(1) ባለሥልጣኑ የካፒታል ገበያ ግብይት መረጃን ከሁሉም ቁጥጥር የሚደረግባቸው ሰዎች ይሰበስባል።

(2) ሁሉም ቁጥጥር የሚደረግባቸው ሰዎች አመታዊ የግብይት መዛግብት ሪፖርቶችን ባለሥልጣኑ በሚጠይቀው ሁኔታ ለባለስልጣኑ ማቅረብ አለባቸው።

## ክፍል ሁለት

## የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች ክፍያዎች

### 5. የማመልከቻ ክፍያ

የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪነት ፈቃድ ከባለሥልጣኑ የሚጠይቁ አመልካቾች በሚከተለው የክፍያ ሰንጠረዥ መሰረት የማይመለስ የማመልከቻ ክፍያ ይከፍላሉ።

| ተ.ቁ | የአገልግሎት ፈቃድ አይነት | የማመልከቻ ክፍያ (ብር) |
|---|---|---|
| 1 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገማች ድርጅቶች | 60,000 |
| 2 | የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ስራ አከናዋኝ | 60,000 |
| 3 | ብድር የመመለስ ብቃት ምዘና አገልግሎት ሰጪ ኤጀንሲ | 60,000 |
| 4 | ክራውድ ፈንዲንግ አገናኝ | 60,000 |
| 5 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ጠባቂ | 60,000 |
| 6 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ዲጂታል ንዑስ-ደላላዎች | 60,000 |
| 7 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ፖርትፎሊዮ ሥራ አስኪያጅ | 60,000 |
| 8 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ኢንቨስትመንት አማካሪ (ድርጅት) | 60,000 |
| 9 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ኢንቨስትመንት አማካሪዎች (ግለሰብ) | 30,000 |
| 10 | የኢንቨስትመንት ባንክ (የባንክ ቡድን አባል የሆነ) | 60,000 |
| 11 | የኢንቨስትመንት ባንክ (የባንክ ቡድን አባል ያልሆነ) | 60,000 |
| 12 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ሮቦ አማካሪ | 60,000 |
| 13 | የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ | 60,000 |
| 14 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ አከናዋኝ | 60,000 |

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን

| | | |
|---|---|---|
| 15 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ሽሪአ አማካሪ (ድርጅት) | 60,000 |
| 16 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ሽሪአ አማካሪ (ግለሰብ) | 30,000 |
| 17 | ተጂሚ እንደራሴዎች | 5,000 |

**6. የፈቃድ ክፍያ**

የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ፈቃዱ በባለሥልጣኑ ሲፀድቅ የማይመለስ የፈቃድ ክፍያ በሚከተለው መልኩ ይከፍላል።

| ተ.ቁ | የአገልግሎት ፈቃድ | የፈቃድ ክፍያ (ብር) |
|---|---|---|
| 1 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገማች ድርጅቶች | 330,000 |
| 2 | የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ስራ አከናዋኝ | 540,000 |
| 3 | ብድር የመመለስ ብቃት ምዘና አገልግሎት ሰጪ ኤጀንሲዎች | 330,000 |
| 4 | ክራውድ ፈንዲንግ አገናኞች | 132,000 |
| 5 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ጠባቂ | 1,000,000 |
| 6 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ዲጂታል ንዑስ-ደላላዎች | 132,000 |
| 7 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ፖርትፎሊዮ ሥራ አስኪያጆች | 330,000 |
| 8 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ኢንቨስትመንት አማካሪዎች (ድርጅት) | 240,000 |
| 9 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ኢንቨስትመንት አማካሪዎች (ግለሰብ) | 60,000 |
| 10 | የኢንቨስትመንት ባንክ (የባንክ ቡድን አባል የሆነ) | 1,000,000 |
| 11 | የኢንቨስትመንት ባንክ (የባንክ ቡድን አባል ያልሆነ) | 540,000 |
| 12 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ሮቦ አማካሪ | 120,000 |
| 13 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ደላላ | 132,000 |
| 14 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ አከናዋኝ | 240,000 |
| 15 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ሽሪአ አማካሪ (ድርጅት) | 240,000 |
| 16 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ሽሪአ አማካሪ (ግለሰብ) | 60,000 |

| | | |
|---|---|---|
| 17 | ተሿሚ እንደራሴዎች | 10,000 |

## 7. የፈቃድ እድሳት ክፍያዎች

ሁሉም የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪዎች አመታዊ የፈቃድ እድሳት ክፍያን እንደሚከተለው ይከፍላሉ።

| ተ.ቁ | የአገልግሎት ፈቃድ አይነት | የዕድሳት ክፍያ (ብር) |
|---|---|---|
| 1 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገማች ድርጅቶች | 165,000 |
| 2 | የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ስራ አከናዋኝ | 270,000 |
| 3 | ብድር የመመለስ ብቃት ምዘና አገልግሎት ሰጪ ኤጀንሲዎች | 165,000 |
| 4 | ክራውድ ፈንዲንግ አገናኞች | 66,000 |
| 5 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ጠባቂ | 500,000 |
| 6 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ዲጂታል ንዑስ-ደላላዎች | 66,000 |
| 7 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ፖርትፎሊዮ ሥራ አስኪያጆች | 165,000 |
| 8 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ኢንቨስትመንት አማካሪዎች (ድርጅት) | 120,000 |
| 9 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ኢንቨስትመንት አማካሪዎች (ግለሰብ) | 30,000 |
| 10 | የኢንቨስትመንት ባንክ (የባንክ ቡድን አባል የሆነ) | 500,000 |
| 11 | የኢንቨስትመንት ባንክ (የባንክ ቡድን አባል ያልሆነ) | 270,000 |
| 12 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ሮቦ አማካሪ | 60,000 |
| 13 | የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ደላላ | 66,000 |
| 14 | የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ገበያ አከናዋኝ | 120,000 |
| 15 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ሸሪአ አማካሪ (ድርጅት) | 120,000 |
| 16 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ሸሪአ አማካሪ (ግለሰብ) | 30,000 |
| 17 | ተሿሚ እንደራሴዎች | 5,000 |



የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን

8. ለተቿሚ እንደራሴዎች - የዝውውር ክፍያ

አንድ ተቿሚ እንደራሴ ቅጥሩን ከአንድ የካፒታል ገበያ አገልግሎት ሰጪ ወደ ሌላ ሲቀይር የዝውውር ክፍያን በሚከተለው መልኩ ይከፍላል።

| ለተቿሚ እንደራሴዎች የዝውውር ክፍያ (የኢትዮጵያ ብር) | |
|---|---|
| ተቿሚ እንደራሴ | 5,000 |

## ክፍል ሶስት

## የገበያ መሰረተ ልማት አገልግሎት ሰጪዎች ፈቃድ ክፍያዎች

9. የማመልከቻ ክፍያ

የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ፣ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ እና የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ የማይመለስ የአንድ ጊዜ የፈቃድ ማመልከቻ ክፍያ እንደሚከተለው ይከፍላል።

| ተ.ቁ | የአገልግሎት ፈቃድ | የፈቃድ ክፍያ (ብር) |
|---|---|---|
| 1 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ | 500,000 |
| 2 | ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ | 500,000 |
| 3 | የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ | 500,000 |

10. የፈቃድ ክፍያ

የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ፣ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ እና የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ የማይመለስ የአንድ ጊዜ የፈቃድ ማመልከቻ ክፍያ እንደሚከተለው ይከፍላል።

| ተ.ቁ | የአገልግሎት ፈቃድ | የፈቃድ ክፍያ (ብር) |
|---|---|---|
| 1 | የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ | 1,500,000 |

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን

| | | |
|---|---|---|
| 2 | ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ | 1,500,000 |
| 3 | የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ | 1,500,000 |

**11. ዓመታዊ የፈቃድ እድሳት ክፍያ**

የሰነደ ሙዓለ ንዋይ ገበያ፣ ያልተማከለ የጠረጴዛ ዙሪያ ገበያ እና የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች አስቀማጭ እና ክፍያ አጣሪና ፈጻሚ ኩባንያ አመታዊ የፈቃድ እድሳት ከጠቅላላ ያልተጣራ አመታዊ ገቢው 1% ይከፍላል።

## ክፍል አራት

## የሰነደ ሙዓለ ንዋዮች ምዝገባ የማመልከቻ እና የመመዝገቢያ ክፍያዎች

**12. አክሲዮኖች**

በአዋጁ አንቀፅ 75 መሰረት የደንበኛ ሳቢ መግለጫ መገምገም እና ማፅደቅን ያካተተ አክሲዮን ለመመዝገብ የማመልከቻ እና የምዝገባ ክፍያዎች እንደሚከተለው ይሆናሉ።

| **የአክሲዮን ምዝገባ (ብር)** | |
|---|---|
| የማመልከቻ ክፍያ | 300,000 |
| የመመዝገቢያ ክፍያ | ከጠቅላላው ለሽያጭ ከቀረቡት አክሲዮኖች ዋጋ 0.1% |

**13. የቋሚ ገቢ ሰነደ ሙዓለ ንዋይ**

(1) የኩባንያ ቦንዶች፡-

በአዋጁ አንቀፅ 75 መሰረት የደንበኛ ሳቢ መግለጫ መገምገም እና ማፅደቅን ያካተተ የቋሚ ገቢ ሰነደሙዓለ ንዋይ ለመመዝገብ የማመልከቻ እና የምዝገባ ክፍያዎች እንደሚከተለው ይሆናሉ።

| **የኩባንያ ቦንዶች ምዝገባ (ብር)** | |
|---|---|
| የማመልከቻ ክፍያ | 150,000 |
| የመመዝገቢያ ክፍያ | ከጠቅላላው ለሽያጭ ከቀረበው ቦንድ ዋጋ |

| | |
|---|---|
| | 0.05% |

(2) የአካባቢ አስተዳደሮች ቦንዶች

በአካባቢ አስተዳደሮች የሚወጡ የቋሚ ገቢ ሰነደ ሙዓለንዋዮች የማመልከቻ እና ምዝገባ ክፍያ እንደሚከተለው ይሆናል።

| **የአካባቢ አስተዳደሮች ቦንድ ምዝገባ (ብር)** | |
|---|---|
| የማመልከቻ ክፍያ | 50,000 |
| የመመዝገቢያ ክፍያ | ከጠቅላላው ለሽያጭ ከቀረበው ቦንድ ዋጋ 0.025% |

14. **የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ**

የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ የማመልከቻ እና ምዝገባ ክፍያ እንደሚከተለው ይሆናል።

| **የጋራ ኢንቨስትመንት ፈንድ ምዝገባ (ብር)** | |
|---|---|
| የማመልከቻ ክፍያ | ብር 150,000 |
| የመመዝገቢያ ክፍያ | ከጠቅላላ ለሽያጭ ከቀረበው ሰነደ ሙዓለንዋይ ወይም ክፍልፋዮች የአቅርቦቱ ዋጋ 0.1% |

**<u>ክፍል አምስት</u>**

**<u>የግብይት ክፍያዎች</u>**

15. **የግብይት ክፍያዎች**

የግብይት ክፍያዎች እንደሚከተለው ይሆናሉ።

| **የግብይት አይነት/ሰነድ** | **የግብይት ክፍያ** |
|---|---|
| የቋሚ ገቢ ሰነደ ሙዓለንዋዮች | የግብይቱን ዋጋ 0.005% |

| | |
|---|---|
| አክሲዮኖች | የግብይቱን ዋጋ 0.15% |

## ክፍል ስድስት

### ልዩ ልዩ

**16. የክፍያ ጊዜ**

(1) የማመልከቻ ክፍያዎች ማመልከቻው በሚቀርብበት ጊዜ ይከፈላሉ።

(2) የፈቃድ እና የምዝገባ ክፍያዎች የሚከፈሉት ፈቃዱ ወይም ምዝገባው በሚፀድቅበት ጊዜ ይሆናል።

(3) የፈቃድ እድሳት ክፍያ ፈቃዱ በባለስልጣኑ ሲታደስ ይከፈላል።

**17. ከአንድ በላይ ለሆኑ ፈቃዶች የሚከፈል ክፍያ**

ከአንድ በላይ ፈቃድ ለማግኘት የሚያመለክት አመልካች ለእያንዳንዱ ፈቃድ ሁሉንም አግባብነት ያላቸውን ክፍያዎችን መክፈል ይኖርበታል።

**18. የአስተዳደር ክፍያዎች**

ባለሥልጣኑ የማባዣ እና ምትክ የፈቃድ ሰርተፍኬት ለመስጠት እና ሌሎች መሰል አስተዳደራዊ አገልግሎቶችን ለመስጠት የሚወጡ ወጪዎችን ለመሸፈን የሚሆኑ ልዩ ልዩ አነስተኛ የአስተዳደር ክፍያዎችን ዝርዝር በድረ-ገጹ ላይ ያሳውቃል።

**19. መዛግብት**

(1) ከፋዮች ቢያንስ ለአስር አመታት ትክክለኛ የክፍያ ሰነዶችን እና ማህደሮችን ጠብቀው መያዝ አለባቸው።

(2) ከፋዮች ማናቸውንም ከክፍያ ጋር የተያያዙ አስፈላጊ ሰነዶች እና መረጃዎችን በባለስልጣኑ በተጠየቁ ጊዜ ሁሉ ማቅረብ አለባቸው።

**20. ባለስልጣኑ በቦርዱ ውሳኔ መሰረት ማናቸውንም ክፍያዎች ለጊዜው ሊተው ወይም ሊቀንስ ስለሚችልበት ሁኔታ**

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን

ባለሥልጣኑ የካፒታል ገበያውን እድገት እና የተሳታፊዎችን አቅም ከግምት በማስገባት እንዲሁም የገበያ ተሳትፎን ለማሳደግ ሲባል አስቀድሞ ቦርዱ በሚሰጠው ውሳኔ መሰረት በዚህ መመሪያ የተደነገጉትን ማናቸውንም ክፍያዎች ለጊዜው ሊተው ወይም ሊቀንስ ይችላል።'

21. **መመሪያው የሚጸናበት ቀን**

ይህ መመሪያ በፍትሕ ሚኒስቴር ከተመዘገበበት እና በባለሥልጣኑ ድረ-ገጽ ላይ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል።

አዲስ አበባ
መጋቢት፣ 2016 ዓ.ም
ዶ/ር ብሩክ ታዬ
ዋና ዳይሬክተር
የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን

የኢትዮጵያ የካፒታል ገበያ ባለስልጣን